**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות לבתי ספר על-יסודיים

מועד הבחינה: קיץ תשע"ו, 2016

**מספר השאלון: 29108**

**תרגום לאמהרית (6)**

# ת ו ל ד ו ת   ע ם   י ש ר א ל

## לעולים חדשים

## בבתי ספר דתיים

## חלק א

יחידת לימוד אחת

**הוראות לנבחן**

א. משך הבחינה: שעה וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה שלושה פרקים.

פרק ראשון – בפרק זה שלושה נושאים:

I: תקופת בית שני

II: הקהילה היהודית בימי הביניים

III: החסידות

בנושא שלמדת עליך לענות על שתי שאלות — (16x2) — 32 נקודות

פרק שני – בפרק זה עליך לענות על שלוש שאלות — (16x3) — 48 נקודות

פרק שלישי – בפרק זה עליך לכתוב על ארבעה מושגים/שמות – (5x4) –20 נקודות

סה"כ — 100 נקודות

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. הוראות מיוחדות:

(1) כתוב על כריכת המחברת את הנושא שלמדת.

(2) בתשובתך הבא עובדות ואל תסתפק בהערכות כלליות.

כתוב במחברת הבחינה בלבד, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב כטיוטה (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).

רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**ב ה צ ל ח ה !**

---

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ጊዜ፦ የ2016 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 29108**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የሕዝበ እስራኤል ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

## በሃይማኖተኞች ት/ቤቶች ለሚማሩ

## ክፍል አ

ባለ አንድ ነጥብ ትምህርት

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

አ. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ አንድ ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ፦ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎች ይዟል።

ምዕራፍ አንድ – ይህ ምዕራፍ ሦስት ርዕሶችን ይዟል፦

I፦ የሁለተኛው ቤተመቅደስ ወቅት

II፦ የይሁዳውያን ማኅበረሰብ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን

III፦ "ሐሲዳዊነት" (החסידות)

ከተማርከው ርዕስ ሁለት ጥያቄዎችን መመለስ አለብህ

– (2×16) – 32 ነጥብ

ምዕራፍ ሁለት – በዚህ ምዕራፍ ሦስት ጥያቄዎችን መመለስ ይኖርብሃል

– (3×16) – 48 ነጥብ

ምዕራፍ ሦስት – በዚህ ምዕራፍ ስለ አራት ፅንሰ-ሀሳቦች/ስሞች መጻፍ አለብህ

– (4×5) – 20 ነጥብ

በአጠቃላይ – 100 ነጥብ

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. ልዩ መመሪያዎች፦

(1) የተማርከውን ርዕስ በደብተሩ ሽፋን ላይ ጻፍ።

(2) በመልስህ ላይ ተጨባጭ እውነታዎችን አሳይ፥ ጠቅለል ባለ መልስ አታብቃ።

እንደ ንድፍ (טיוטה) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ የሒሳብ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ።

በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

## ምዕራፍ አንድ (32 ነጥብ)

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሦስት ርዕሶች አሉ፦

ርዕስ I፦ የሁለተኛው ቤተመቅደስ ወቅት

ርዕስ II፦ የይሁዳውያን ማኅበረሰብ በመካከለኛው ክፍል ዘመን

ርዕስ III፦ "ሐሲዳዊነት" (החסידות)

ከተማርከው ርዕስ ብቻ የሆኑትን ጥያቄዎች ባላቸው ትዕዛዛት መሠረት መልስ።

### ርዕስ I፦ የሁለተኛው ቤተመቅደስ ወቅት

የተማርከው ይህን ርዕስ ከሆነ ፥ ከ1-4 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን መልስ።
(ለእያንዳንዱ ጥያቄ 16 ነጥብ)

1. ሄሮድስ በይሁዳዊያን ላይ ያደረገውን አንድ ድርጊት እና ይሁዳዊያን ባልሆኑት ላይ ያደረገውን አንድ ድርጊት **አቅርብ**።
   በአንዱ ድርጊት በኩል የሄሮድስን ዓላማ **አብራራ**።
2. ይሁዳዊያን ገሊልን ለመከላከል/ለማዳን (በ67 ለቀጠራው) ያልቻሉበትን አንድ ምክንያት **አቅርብ** እና የዚህ የገሊል ውድቀት በእየሩሳሌም ማህበራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ ላይ ምን ተጽዕኖ እንዳደረገ **አብራራ**።
3. በመጀመሪያዎቹ ገዢዎች ወቅት ይሁዳ የነበራትን መብት/ቦታ **አቅርብ**። ይህ ለገዢዎቹ የተሰጠው መብት ወይም ኃላፊነት በይሁዳዊያን ሠፋሪዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ እንዴት እንዳስቻላቸው **አብራራ**።
4. ቤተ መቅደሱ ከፈረሰ በኋላ ሕዝቡን አንድ ለማድረግ "ራባን" ጋምልኤል ያደረጋቸውን ሁለት ድርጊቶች **አቅርብ**።

### ርዕስ II፦ የይሁዳውያን ማኅበረሰብ በመካከለኛው ክፍል ዘመን

የተማርከው ይህን ርዕስ ከሆነ ከ5-8 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን መልስ።
(ለእያንዳንዱ ጥያቄ 16 ነጥብ)

5. በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የማኅበረሰቡን ኃላፊነት መሠረታዊ ደንብ እና መሠረታዊ ሥነ-ምግባር **አቅርብ**።
6. በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከገቢ ግብር ነጻ መሆንን የጠየቁትን ሁለት የይሁዳዊያን ቡድኖችን **ጥቀስ**። ለዚህ አቤቱታ አንዱ ቡድን ያቀረበውን ማስረጃ/ማሳመኛ **አቅርብ**።
7. በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ለይሁዳዊያን ማኅበረሰብ ተቋማት መብዛት ሁለት ምክንያቶችን **አቅርብ**።
8. በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአሽከናዚ (אשכנז) ይሁዳዊያን ሕዝብ ማኅበራዊ አገነባብ ማኅበረሰቡ በተመሠረተበት መንገድ እና ከክርስትና ማኅበረሰብ የግንባታ መልክ ተጽዕኖ ደርሶበታል። ይህን ውሳኔ **አብራራ**።

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ርዕስ III፦ "ሐሲዳዊነት" (החסידות)

የተማርከው ይህን ርዕስ ከሆነ ፣ ከ9-12 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን መልስ። (ለእያንዳንዱ ጥያቄ 16 ነጥብ)

**9.** ከ"הלבבמה" በፊት በነበረው ወቅት ፖላንድ ውስጥ በይሁዳዊያን ማኅበረሰብ ዘንድ ለቶራ ትምህርት (תלמוד תורה) ለነበረው አስፈላጊነት አንድ ምሳሌ **አቅርብ**።
በዚሁ ወቅት ለጋራ ዋስትና (ערבות הדדית) ሃሳብ ለነበረው አስፈላጊነት አንድ ምሳሌ **አቅርብ**።

**10.** ከ"הלבבמה" በኋላ በፖላንድ ውስጥ በነበሩት ይሁዳዊያን ማኅበረሰብ ለነበረው ማኅበራዊ ውጥረት (מתח) ምክንያት የሆኑትን ሁለቱን **አቅርብ**።

**11.** "ታማኝነት" ("דבקות") የሚለውን ራእይ **ግለጽ** እና ሰው ወደ ታማኝነት ለመድረስ በማንነቱ ላይ ማምጣት የሚገባውን ለውጦች **አብራራ**።

**12.** "ተቃዋሚዎች" በሐሲዳዊያን ላይ ያላቸውን ሁለት ማሳመኛዎች/ተቃውሞዎች እና በሐሲዳዊያን ላይ ያደረጉትን አንድ ድርጊት **አቅርብ**።

## ምዕራፍ ሁለት (48 ነጥብ)

ከ13-18 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ። (ለእያንዳንዱ ጥያቄ 16 ነጥብ)

**13.** የነፃ መውጣቱ (ኢማኒስፔሽኑ) ሂደት በይሁዳዊያን ፊት አዳዲስ አማራጮች/ዕድሎችን ከፍቷል። የዚህን ዓይነት አንድ አማራጭ **ጥቀስ**። ከሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ስለ ነፃ መውጣቱ ሂደት የሰጠውን ምላሽ **አብራራ**።

**14.** በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በነበረው ዘረኝነት እና በአሁኑ በአዲሱ ወቅት ባለው ዘረኝነት መካከል ያለውን አንድ ልዩነት **አቅርብ**።
በ19ኛው መቶ አንድ የዘረኝነት መግለጫ ከምስራቅ ወይም ከምዕራብ አውሮፓ **አቅርብ**።

**15.** የሃባሮን ሮቺልድን ሕጋዊ ሞግዚት (אפוטרופסות) ዘዴ በመቃወም የቀረቡ ሁለት ማሳመኛዎችን **አብራራ**።

**16.** የሄርጸልን አንድ ድርጊት **ጥቀስ** እና የጠቀስከው ድርጊት የይሁዳዊያንን ብሔርተኝነት ለማካሄድ እንዴት እንደረዳ አብራራ።

**17.** "ሀሚዝራሂ" ("המזרחי") የተባለውን እንቅስቃሴ መነሻ **አብራራ**። የእንቅስቃሴውን አንድ ሃሳብ "ሃኮል ሃኮሬ" ("הקול הקורא") ከሚለው ውስጥ **አቅርብ**።

**18.** የ"ቋንቋዎችን ጦርነት" ("የቋንቋን ጥል") **አቅርብ**።
ይህ ጉዳይ በሁለተኛው ዙር ወደ እስራኤል በመጡት (העלייה השנייה) አዲስ ገቢዎች ዘንድ ለምን አስፈላጊ እንደነበር **አብራራ**።

**(ልብ በል፦ ምዕራፍ ሦስት በሚቀጥለው ገጽ ላይ ነው)።** /ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሦስት (20 ነጥብ)

በፊትህ ከ(19-25) የተሰጡ ሰባት ጽንሰ-ሀሳቦች/ስሞች አሉ፣ በእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ክፍሎች ይገኛሉ።

ከፅንሰ-ሀሳቦቹ / ከስሞቹ <u>አራቱን</u> ምረጥ እና ከመረጥከው እያንዳንዱ ፅንሰ-ሀሳብ/ስም ጋር ግንኙነት ባላቸው <u>ሁለት</u> ክፍሎች ላይ መልስ ስጥ (ለእያንዳንዱ ፅንሰ-ሀሳብ/ስም 5 ነጥብ)።

**19.** <u>"ሃኻም ባአሺ" (חכם באשי)</u>

— የ"ሃኻም ባአሺ" የሥራ ድርሻ ምን ነበር?

— እስከ የትኛው ወቅት ነው ይህ የሥራ ድርሻ (משׂרה) የቀየው?

**20.** <u>"ክፍፍሉ" (החלוקה)</u>

— የአሮጌው ሠፈራ ሰዎች ለምንድን ነው በስደት ያሉ ይሁዳዊያን በእስራኤል ምድር ያሉ ሠፈራዎችን (የሹቪም) በኢኮኖሚ የመደገፍ ግዴታ አለባቸው ብለው የሚያስቡት?

— የክፍፍሉ ገንዘብ በአሽካናዚዎች ዘንድ እንዴት ተከፋፈለ? እና እንዴትስ ነው ስፋራዲዎች ዘንድ የተከፋፈለው?

**21.** <u>ከግንቡ ውስጥ መውጣት (היציאה מן החומות)</u>

— "ከግንቡ ውስጥ መውጣት" ማለት ምንድን ነው?

— የዚህ ሂደት ዕቅድ አቅራቢዎች እነማን ናቸው?

**22.** <u>የዊልሰን 14 ነጥቦች (14 הנקודות של וילסון)</u>

— የዊልሰን 14 ነጥቦች እቅድ ዓላማ ምን ነበር?

— በእቅዱ ይህን ዓላማ የሚገልጹትን <u>ሁለት</u> ነጥቦች ጥቀስ።

**23.** <u>ኒ.ሊ.ይ. (ני"לי)</u>

— የני"לי ድርጅት በየትኛው ወቅት ነው የሠራው? እና ዓላማውስ ምን ነበር?

— የድርጅቱ አባላት ዕጣ ፋንታ ምን ሆነ?

**24.** <u>የቨርሳይ ስምምነት (חוזה ורסאי)</u>

— የቨርሳይ ስምምነት መቼ ተፈረመ?

— ከቨርሳይ ስምምነት <u>ሁለት</u> አንቀጾችን አሳይ።

**25.** <u>የባልፉር አዋጅ (הצהרת בלפור)</u>

— የባልፉር አዋጅ ለማን ነው የተላከው? እና ለይሁዳውያንስ አስፈላጊነቱ ምን ነበር?

— በእስራኤል ምድር ለሚኖሩ ይሁዳውያን ያልሆኑትን ነዋሪዎች በተመለከተ በአዋጁ ምን ተባለ? እና ከእስራኤል ምድር ውጪ ስለሚኖሩ ይሁዳውያንን ሁኔታ በተመለከተ ምን ተባለ?

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך